የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 24
ADDIS ABABA, 10th March, 2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፭/፪ሺ፱ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ……………………………………………………………ገጽ ፱ሺ፭፻፷፭

**CONTENT**

Proclamation No. 995/2017
Ethiopian Youth Revolving Fund Establishment Proclamation ……………………………………………………..Page 9565

### አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፭/፪ሺ፱

### የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የልማት ግቦቻችን ስኬት በሀገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የወጣቶችን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ፤

የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ተደራጅተው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲያቃልሉ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ወጣቶች ያላቸውን ዕምቅ የማምረት አቅም ተጠቅመው በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን እንዲችሉ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ድጋፍ ለማቅረብ የወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

### PROCLAMATION No. 995/2017

### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN YOUTH REVOLVING FUND

**WHEREAS,** the attainment of our development objectives requires the direct participation of youth in the economic activities of our country;

**WHEREAS,** it is necessary to provide youth with financial and technical support to help them alleviate their economic and social problems through engagement in organized income generating activities with a view to ensuring their all-rounded participation and benefit;

**WHEREAS,** to make available the financial resource needed to enable youth realize their productive potential and become direct participants in the economic activities of our country, it is necessary to establish the Youth Revolving Fund;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍልአንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፭/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው፤

፪/ "ተጠቃሚዎች" ማለት በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት ከፈንዱ ተጠቃሚ የሚሆኑ በጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ሥር የተደራጁ ወጣቶች ናቸው፤

፫/ "ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ" ማለት የፌደራል ከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲን ለማቋቋም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፸፬/፪ሺ፰ አንቀጽ ፪(፫) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

፬/ "አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት" ማለት በአነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፮/፪ሺ፩ አንቀጽ ፪(፲፩) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

፭/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፮/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከቱት ክልሎች ሲሆኑ፣የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፯/ "ወጣት" ማለት በአሥራ ስምንት እና በሰላሳ አራት



## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Youth Revolving Fund Establishment Proclamation No. 995/2017".

**2. Definition**

In this Proclamation:

1/ "Bank" means the Commercial Bank of Ethiopia;

2/ "beneficiaries" means youth organized under micro enterprises who qualify to benefit from the fund in accordance with the criteria set out in this Proclamation and the directive to be issued hereunder;

3/ "micro enterprise" shall have the meaning provided under Article 2(3) of the Federal Urban Job Creation and Food Security Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 374/2016;

4/ "micro financing institutions" shall have the meaning provided under Article 2(11) of the Micro Financing Business Proclamation No. 626/2009;

5/ "Ministry or Minister" means the Ministry or the Minister of Finance and Economic Cooperation, respectively;

6/ "State" means any Regional State referred to under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

7/ "youth" means any male or female of Ethiopian Nationality falling within the age range of eighteen to thirty four;

ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወንድ ወይም ሴት ነው፤



፰/ “አግባብ ያለው ባለሥልጣን” ማለት በማናቸውም ስያሜ ቢጠራም የወጣቶችን ጉዳይ በሚመለከት ስልጣን የተሰጠው የክልል መንግሥት አካል ነው፤

፱/ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ፫. <u>መቋቋም</u>

፩/ የኢትዮጵያ ወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ (ከዚህ በኋላ “ፈንድ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪ ፈንዱ ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ለፈንዱ ዓላማዎች ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

## ፬. <u>የፈንዱ ዓላማዎች</u>

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ ወጣቶች ያላቸውን አቅም ለሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲያውሉ እገዛ ማድረግ፤

፪/ ወጣቶች ተደራጅተው ለሚያካሂዱቸው ገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች የገንዘብ ድጋፍ መስጠት፤

፫/ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡

## ፭. <u>የፈንዱ ምንጭ</u>

የፈንዱ ምንጭ ከፌደራል መንግሥት የሚመደብ በጀት ይሆናል፡፡

## ፮. <u>የፈንዱ መጠን</u>

፩/ የፈንዱ መጠን ብር ፲ ቢሊዮን (አሥር ቢሊዮን) ነው፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ፈንዱን እንዲያስተዳድር የተሰየመው አካል በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የፈንዱን ገንዘብ ከተ



8/ “appropriate authority” means an authority of a state, whatever its designation, that is in charge of youth affairs;

9/ any expression in the masculine gender shall include the feminine.

## 3. <u>Establishment</u>

1/ There is hereby established the Ethiopian Youth Revolving Fund (herein after referred to as “the Fund”).

2/ The fund shall serve as a permanent source of finance to be used in furtherance of the objectives of the Fund.

## 4. <u>Objectives of the Fund</u>

The Fund shall have the following objectives:

1/ assist youth to employ their capabilities in creating job opportunities;

2/ provide financial assistance for organized income generating activities conducted by youth;

3/ ensure the all-rounded participation and benefit of youth.

## 5. <u>Source of the Fund</u>

The source of the Fund shall be budget allocated by the Federal Government.

## 6. <u>Amount of the Fund</u>

1/ The amount of the fund shall be 10 billion (ten billion) Birr.

2/ The Minister is hereby authorized to transfer from the consolidated fund, the proceeds of the fund to the body entrusted by Article 7 of this Proclamation to administer the fund.

## <u>PART TWO</u>

## <u>ADMINISTRATION OF THE FUND</u>

## 7. <u>Responsibility to administer the Fund</u>

The Bank is hereby entrusted with the responsibility to

ጠቃለለው ፈንድ ውስጥ እንዲያስተላልፍ ተፈቅዷል፡፡

## ክፍል ሁለት

### የፈንዱ አስተዳደር

**፯. ፈንዱን የማስተዳደር ኃላፊነት**

ባንኩ በፌደራል መንግሥት ስም ፈንዱን የማስተዳደር  በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፰. የፈንዱ አጠቃቀም**

፩/ የፈንዱ ገንዘብ ለሚከተሉት ዓላማዎች ይውላል፦

ሀ) ተጠቃሚዎች ለሚያቀርቧቸው አግባብ ባለው ባለሥልጣን እና በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም በባንኩ ድጋፍ ያገኙ የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ የካፒታል ንብረቶችን ለማቅረብ፣

ለ) ለፕሮጀክቶች የሥራ ማስኬጃ ወጪ፡፡

፪/ የፈንዱ ገንዘብ የተዘዋዋሪ ፈንድ ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ለተጠቃሚዎች በብድር ይተላለፋል፡፡

**፱. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት**

ሚኒስቴሩ፣

፩/ የየክልሉን ወጣቶች ቁጥር መሠረት በማድረግ ከፈንዱ ገንዘብ ላይ ለየክልሉ ሊከፋፈል የሚገባውን ድርሻ በማስላት ለባንኩ ያሳውቃል፤

፪/ ባንኩ የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚዎች የሚያስተላልፍበትን ደንቦችና ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይወስናል፤

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯(፪) መሠረት ከባንኩ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ከተጠቃለለው ፈንድ ላይ ክፍያ ይፈጽማል፤

administer the Fund on behalf of the Federal Government. 

**8. Utilization of the Fund**

1/ The Fund's money shall be used for the following purposes:

a) for the supply of capital goods necessary for implementing income generating projects proposed by beneficiaries which are supported by the appropriate authority and the micro financing institutions or the bank;

b) to cover operating costs of the projects.

2/ The proceeds of the fund shall be transferred to beneficiaries on loan basis in accordance with the scheme of revolving fund.

**9. Duties and responsibilities of the Ministry**

The Ministry shall:

1/ calculate and communicate to the bank the share of each state from the proceeds of the fund on the basis of the size of the youth population of each state;

2/ determine, in consultation with the appropriate entities, the terms and conditions under which the bank transfers the proceeds of the fund to beneficiaries through micro financing institutions;

3/ disburse the proceeds of the fund to the bank upon request from the bank pursuant to Article 6(2) of this Proclamation;

4/ integrate the statement and reports on the utilization of the proceeds of the fund received from the bank into the consolidated financial report of the Government and submit same to the Council of Ministers and the House of Peoples Representatives, respectively.

፫/ ከባንኩ የሚደርሰውን የፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም መግለጫና ሪፖርት በተጠቃለለው ዓመታዊ የመንግሥት ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ በማካተት በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡



**፲. <u>የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ባንኩ፡-

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱(፩) እና (፪) መሠረት የፈንዱን ገንዘብ በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በኩል ለተጠቃሚ ዎች ያስተላልፋል፤

፪/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩(፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት በሌሉባቸው አካባቢዎች ቅርንጫፍ ባንኮቹ የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተክተው እንዲሰሩ ያደርጋል፤

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩(፪) መሠረት ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቀርብለትን ሪፖርት በማጠቃለል በየስድስት ወሩ፣ እንዲ ሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭(፪) መሠረት የተመረመረ የፈንዱን ሂሣብ ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በየዓመቱ ሂሣቡ በተመረመረ በአንድ ወር ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

**፲፩. <u>የአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት</u>**

አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት፡-

፩/ የተጠቃሚዎች የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክት አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተገምግሞና ተደግፎ



**10. <u>Duties and responsibilities of the Bank</u>**

The Bank shall:

1/ transfer the proceeds of the fund to beneficiaries through micro financing institutions in accordance with Article 9(1) and (2) of this Proclamation;

2/ without prejudice to the provision of Article 11(1) of this Proclamation, carry out through its branches the functions of micro financing institutions in places where micro financing institutions are not available;

3/ submit to the Ministry every six month a consolidate report of the utilization of the proceeds of the fund it receives from micro financing institutions pursuant to Article 11(2) of this Proclamation and also submit annually to the Ministry an audited statement of the funds' finance together with the audit findings in accordance with Article 15(2) of this Proclamation within one month of the carrying out of the audit.

**11. <u>Duties and responsibilities of micro financing institutions</u>**

The micro financing institutions shall:

1/ enter into an agreement with and provide the required amount of loan to beneficiaries in accordance with the terms and conditions set out by the Ministry upon receipt of income generating project documents of beneficiaries evaluated and approved by the appropriate authority and where it is satisfied that the project is feasible;

2/ submit a detailed report on the utilization of the proceeds of the fund to the bank every six month.

ሲቀርብላቸው እና የቀረበው ፕሮጀክት አዋጭ መሆኑን ሲያምኑበት ከተጠቃሚው ጋር ስምምነት በማድረግ ሚኒስቴሩ በሚወስነው የብድር ደንቦችና ሁኔታዎች መሠረት ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን ብድር ለተጠቃሚዎች ያቀርባሉ፤

፪/ ስለፈንዱ ገንዘብ አጠቃቀም ዝርዝር መግለጫ የያዘ ሪፖርት በየስድስት ወሩ ለባንኩ ያቀርባሉ፡፡



## ፲፪. የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር፦

፩/ ከፈንዱ አጠቃቀም ጋር በተገናኘ አግባብ ያላቸው ባለሥልጣናትን የሥራ እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፪/ አግባብ ካላቸው ባለሥልጣናት የሚደርሰውን ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርቶች በመገምገም የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየደረጃው ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

## ፲፫. አግባብ ያለው ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

አግባብ ያለው ባለሥልጣን፦

፩/በዚህ አዋጅ መሠረት ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ ወጣቶችን ይለያል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ወጣቶችን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች ያደራጃል፤

፪/ተጠቃሚዎች የቴክኒክና ሙያ እንዲሁም የንግድ ሥራ ልማት፣ ሥልጠናና ምክር እንዲያገኙ ያደርጋል፤



## 12. Duties and responsibilities of the Ministry of Youth and Sport

The Ministry of Youth and Sport shall:

1/ coordinate the activities of the appropriate authorities with regard to the utilization of the fund and render the necessary assistance thereto;

2/ evaluate the semi-annual and annual reports on the implementation of beneficiaries' projects it receives from the appropriate authorities and submit an annual consolidated report to the Council of Ministers and the House of Peoples' Representatives, respectively.

## 13. Duties and responsibilities of the appropriate authority

The appropriate authority shall:

1/ identify youth qualifying to become beneficiary in accordance with this Proclamation and organize youth under income generating activities where necessary;

2/ facilitate the provision of technical, professional and business development training and consultancy services to beneficiaries;

3/ facilitate the provision of technical assistance to beneficiaries in project preparation;

4/ evaluate, in cooperation with appropriate entities, the income generating project proposals of beneficiaries and communicate the accepted projects with a support document to micro financing institutions or the bank, as the case may be;

5/ follow up and evaluate the execution of beneficiaries' projects; prepare semi-annual and annual reports and submit same to the Ministry

፫/በፕሮጀክቶች ዝግጅት ተጠቃሚዎች የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፬/ተጠቃሚዎች የሚያቀርቧቸውን የገቢ ማመንጫ ፕሮጀክቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይገመግማል፣ ተቀባይነት ያገኙ ፕሮጀክቶችን ከድጋፍ ሰነድ ጋር እንደአግባብነቱ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ለባንኩ ያስተላልፋል፤

፭/ ተጠቃሚዎች የሚያንቀሳቅሷቸውን ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡



**፲፬. የፈንዱ የባንክ ሂሣብ**

የፈንዱ ገንዘብ ሚኒስትሩ በፈንዱ ስም በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሣብ ይቀመጣል፡፡

**፲፭. የፈንዱ የሂሣብ ሰነዶች**

፩/ባንኩ የፈንዱን ሂሣብ በሚመለከት የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት በተለይ ይይዛል፡፡

፪/ የፈንዱ ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፮. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ሚኒስትሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፯. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፰. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

of Youth and Sport.



**14. Account of the Fund**

The proceeds of the fund shall be deposited in special account to be opened for the fund by the Minister.

**15. Books of account of the Fund**

1/ The Bank shall maintain a separate, complete and accurate book of accounts for the account of the Fund.

2/ The account of the Fund shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor appointed by him.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS

**16. Power to issue directive**

The Minister may issue directives that are necessary for the proper implementation of this Proclamation.

**17. Inapplicable laws**

Any Proclamation, Regulation, Directive and practices which are inconsistent with this Proclamation shall not be applicable on matters covered in this Proclamation.

**18. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 10th day of March, 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት